# *“አንድ ዐይና በአፈር አይጫወትም”*

## ይድረስ ለተጋዳላይ ዳዊት ከበደ

“ ጅብ በማያውቁት ሃገር ሂዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ” ይላሉ ቀደምት አባቶቻችን። እንደው ሳስበው ግርም ይለኛል። ደርሶ ቢያዩት ፤ በሰው አምሳል ተፈጥሮ የጅቡን ተግባር ሲፈጽም ቢያገኙት ይመስለኛል ይሄን የማለታቸው መነሻ። ይሄው ጉዳይ ዛሬም አብሮን አለና ብዕሬን ከወረቀቱ ላገናኝ ስሠናዳ ደርሶ በአዕምሮዬ ስንቅር አለ – አወጣሁትናም ጻፍኩት።

ይህችን አስተያየት እጽፍና ርዕሱንም ይሁን ቀዳሚውን ዐረፍተ ነገር እንዲሁ በቆየ አገርኛ ብሂላችን እጠቀም ዘንድ የገፋፋኝ ከሰሞኑ በዚሁ በፈረደበት የኢንተርኔት መረብ ያነበብኩትና እንደጸሃፊው ሁሉ ርዕስ ልሰጠው የተቸገርኩበት “ ጹሁፍ ” ነው። ምንም እንኳ ጸሃፊው ስሙን በ”ጹሁፉ” ግርጌ አላሰፈረውም። ዳሩ እሚያውቃቸው ሰዎች ይህን ገድሉን ያነቡለት ዘንድ ባድራሻቸው ሲሰድ ከግል የኢ–ሜይል ጎተራዬ ተወሽቆ አገኘሁት። ፀሃፊውንም በሚገባ አውቀዋለሁና ዝም ብል ህሊናዬ አይፈቅድም በሚል ሃሳቤን ላጋራው በቀጥታ ከነማዕረጉ በሙሉ ስሙ በድራሻው አቅርቤለታለሁ።

ስለተጋዳላይ ዳዊት ከበደ በቀዳሚነት ብዙም ላስረዳ አልሞክርም። ወደሁኣላ ከነተግባራቱ እመለስበታለሁ። በአሁኑ ወቅት ግን የቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር (KIL) ይባል የነበረው ቡድን አባል መሆኑን ፤ የኢትዮጵያ ነጻ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማህበር አባል ነኝ እንደሚልና EMF የተባለ ድረ ገጽ አዘጋጅ መሆኑን እንደሚናገር መግለጹ ለጉዳዬ መነሻ በቂ ነው እላለሁ። ለተጋዳላይ ዳዊት ይህን እጽፍ ዘንድ መነሻ ሰበብ የሆነው በርሱ ገለጻ አዲስ አባባል በሚል ( የፈጠራ መብቱ ይጠበቅለት) “ የማያድግ ህጻን አይርገምህ ፤ የማይሞት ሽማግሌ አይከዳህ ” ሲል ርዕስ የሰጠው “ ጹሁፍ” ነው። የርዕሱ ትርጉአሜ አልገባኝም። ራሱም ማብራሪያ ስላልሰጠን እንዳልገባው ቀጥሮ ማለቱን መረጥኩ። እኔ ግን እርሱም እኔም ሁላችንም በሚገባን አባባል ተነሳሁ።

ይሄ ሰው በ “ ርዕሱ” ግርጌ ጹሁፉን ስለምን በስሙ ሊያወጣ እንዳልፈለገም አስፍሩአል። ጭብጡ ከግለሰባዊነት ይልቅ የሕዝቡን አመለካከት የሚያንጸባርቅ በመሆኑ በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም አቀረብኩትም ብሉአል። “ ማፈር ድሮ ቀረ” ነው ያሉት? ዕድሜ ሰጥቶን በኢትዮጵያውያን ስም ተጋዳላዮች ሲጽፉ ልናይ ልናነብ በቃን። እርሱ በ ‘ጹሁፉ’ በተጠቀመበት ተራ የጥላቻ ቁንቁአ ሊነቅፍ የጣረው የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ሊቀመንበር ኢ/ር ኃይሉ ሻውልን ነው።

መነሻው እርሱ እንደሚለው  በቅርቡ በአምስት ያመራር አባላት ላይ ያሳለፉት የዕገዳ ደብዳቤ ነው ። በርግጥ ‘ፉሁፋ’ መልስ እንደማያሻው ቢገባኝም ፤ እነህ መስሎቹ በየቦታው እየመሸጉ ነግቶ በጠባ ጥፋትን የዕለት ምግባራቸው አድርገው ስለተያያዙት ሃይ ባይ ያስፈልጋል በሚል እንጂ ።እንደገናም ከተሰማሩበት የጥፋት መንገድ ሊመለሱ ቀርቶ እኩይ ተግባራቸውን እያገዘፉ መሄድ በመምረጣቸው የምናውቃቸው ገመናቸውን ልናጋልጥ ይገባል በሚልም ጭምር ነው። ዳሩ “ፉሁፋ”  መልስ አይገባውም እንጂ ቢያስፈግ እንኩአ ስማቸው የተነሳው ግለሰብ ራሳቸው በሚገባ ጥሩ መልስ ሊሰጡት እንደሚችሉ እምናለሁ።

“ስደት ለወሬ ይመቻል” የሚለውን ሃገርኛ አባባል ለመረዳት ዳዊትን ከማወቅ የበለጠ አስረጂ አይኖርም። ፉሁፋን እያነበብኩ አንዳንዴም ወደትላንቱ የአዲስ አበባ ህይወት ዕዝነ ልቦናዬን እየመለስኩ እንዲሁ ተገረምኩ። ማንኛችሁም “ ጅብ በማያውቁት ሃገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ አለ” ለሚለው ምሳሌ ጥቀሱ ብትባሉ ፈጥናችሁ ዳዊት ብትሉ ስህተተኛ የሚሉአችሁ አብረውት የተሰለፉት ብቻ ናቸው። ይህ እንደውም በስነቃሎቻችን ዙሪያ መዝገበ ቃላት ለሚያዘጋጁ ስሙን እንደምሳሌ ቢያስገቡ ጥሩ አጋጣሚ መሆኑን ብጠቅስም ( አባባሉን ከአንድ የማደንቀው ጸሃፊ መዋሴ ተይዞልኝ) ነገሩን ተጨባጭ ያደርገዋል።

ብዙ ጊዜ ደጋግሜ ራሴን  እጠይቃለሁ። እነአንዳርጋቸው ጽጌ ሰለዘመነ ወያኔ ስንከሳራቸው ጥቂትም ቢሆን ሲጽፉ አብሮአቸው የሚውለው ዳዊት ምነው ይቺን ጉዳይ ይገድፋታል? እያልኩ። የተጋዳላይነት ዘመን ገድልህን በሞቴ ንገረን እስኪ? ታፍራለህ እንዴ? “ያዲያቀነ ሰይጣን. . . “ ሆኖብህ ዛሬም ከተርታ መንደርህ መች ወጣህና ታፍራለህ ። ወያኔና አፍረት አይተዋወቁምና እስኪ ንገረን ። ይሄን ቅንጅት እንዴት እንዳጠመድከው ሳስብ በልደቱ በኩል በመሆኑ ብቻ ትንሽ እፎይ እላለሁ። አየህ የስደትን ደግነት አንተም ተረት አዋቂ ሆንክና “ አዲስ አባባል” ፈጣሪ ለመሆን በቃህ። ከቶ ማን ያውቅህና እንዳሻህ ፈንጭበት የሚሸከምህ ጭንቅላት ካገኘህ። መቼም የብተናው ሃዋሪያ ደቀመዝሙርነትህን በትክክል ያስመሰከርክ ጀግና መሆንህን በአጋጣሚው ሳልገልጥልህ ማለፍ አልወድም።

እስኪ በ”ፉሁፋህ“ ወዳነሳሃቸው አንዳንድ ጉዳዮች ከመግባቴ በፊት ጥቂት አመታትን ወደሁአላ ልውሰድህ። ያች የነበርክባት ኢትዮጵያ ። ትዝ ይልሃል ብዬም ተስፋ አደርጋለሁ። ከረሳሃውም አስታውስሃለሁ። ብዙዎች “ የምናውቅህ “ ስለአንተ እንድንጠይቅ ያደረገችን ዕለት ናትና አትዘነጋም። አዎ! እኔ አልረሳውም ጊዮን ሆቴል ሳባ አዳራሽን ። በጋዜጠኝነት ላይ የተደረገውን ወርክሾፕ ማለቴ ነው። የመወያያ ርዕሱ ካልዘነጋሁት የግሉና የመንግሥት ሚዲያ ጋዜጠኞች  በጋራ ስለምን በሙያ ጉዳይ ሊተባበሩ አይችሉም ? የሚል ነበር።

እንደምታስታውሰው ከርከሩ የጋለ ነበር። በተለይም የመንግስት ተቀጣሪ ጋዜጠኞች ነጻውን ፕሬስ የተቃዋሚ ልሳን አድርገው አለቀቻቸው ስለሚያምኑ መግባባት አልተቻለም ነበር። በአንጻሩ ከነጻው ፕሬስ አባላት በአገዛዙ ላይ ይቀርብ በነበረው ነቀፋ ላይ ያንተን ሚና ልሸሽግ አልችልም። የሁላው ጉድህ ፈላ እንጂ። ታዲያ በመሃል የኢሕአዲግ ልሳን " አብዮታዊ ዲሞክራሲ " ጋዜጣ አዘጋጅና የማአከላዊ ኮሚቴ አባል ሴኩቱሬ ጌታቸው ጉድ አፈላ። ቃል በቃል ባላስታውሰውም ጭብጡን አልዘነጋውም። "እኛ ኢሕአዲጎች ችግር የለብንም ። ለምሳሌ ዳዊት ከበደ ዛሬ እንዲህ ቢናገርም የኛ ጋዜጠኛ ሆኖ ረጅም ጊዜ አብረን ሰርተናል። አሁን የራሱን እየሰራ ነው።ግንኙነታችንም ጥሩ ነው" አለ።

መቼም በዚያች ቅጽበት ሴኩቱሬ ያስቀጠረው ነጥብ አይረሳኝም። ዳዊት በወቅቱ የሰጠህውንስ መልስ ትረሳዋለህ? ግድየለም እኔ አልረሳሁትም ፤ " ሴኮቱሬ ኢዝ ኤ ዲክታተር ፤ ከዲክታተር ጋር እኔ አልሰራም ብለህ ተቀጣህ"። በዚህ ምክንያትም የፓርቲውን ስራ መተውህን ተናገርክ እንጂ የፓርቲ አባልነትህን ስለመተውህና አለመተውህ ግን የተናገርከው እንደሌለ ምንም ሳልቀንስና ሳልጨምር አስታውሳለሁ። ተንቃቃን ፤ ጨዋታው ፈረሰ ዳቦው ተቀረሰ። ብዙዎቻችን በዚያ አዳራሽ ከጎንህ ተቀምጠን የነበርን ብዙ አሰብን። የዚያቸን ዕለት ድንጋጤህንና በግንባርህ የወረደውን ነጭ ላብ መቼውንም አልረሳውም። ጹሁፍህን የማነበው እንግዲህ ይሄን እያስታወስኩ እንደሆነ ያዝልኝ። ዛሬ በተሰለፍክበት ነጻ ፕሬስ ላይ ቀደም ሲል አነጣጥረህ የተኮስከውና ቀጥሎ የለበስከው የበግ ለምድ እንዲሁ በፊቴ ላይ ይመጣል ፤ ታድለህ ከማለት ውጪ ምንም አያስብል ። ሴኮቱሬ መቼም አንተን ተተግኖ ያደረገውን ሰፊ ዲስኩርም አልረሳውም። ከተረሳህ ግድ የለም ወደፊት እመለስበታለሁ።አንተም ለምሳ እንደወጣን ሥራ አለብኝ ብለህ ሳትመለስ ቀረህ።

ልክ ቅንጅትን ስትቀላቀል ወደ ነጻው ፕሬስ ጎራ እንደገባህው ኮቴህ አልተሰማም። ማን አውቀህ? አንድ ጥያቄ ብቻ አንስቼ ይሄን ርዕስ ልቋጭና ወደተነሳሁበት ጭብጥ እመለሳለሁ። እንደው እነዚህ ወያኔ አለቀቻችሁ እንደ አገዳ አኝከው ሲተፉአችሁ ዘላችሁ የምትገቡበት ነጻው ፕሬስም ይሁን የተቃዋሚ ጉዋዳ ታዛቢም ይሁን ተመልካች ያለው አልመስል ያላችሁ ምክንያቱ ምን ይሆን? የሚያሳዝነው ወያኔ ስንኩል ንቀ የጣላችሁ የኢትዮጵያን የነጻነት ትግል እንመራለን ስትሉ ነው። "ማፈር ድሮ ቀረ " ታዲያ ያልተባለ ምን ይባል? አንተና ዙሪያህን ያሉት ማፍረስ የተጣባችሁ ልክፋት ነውና የሚደነቁት የማያውቁአቸው ብቻ ናቸው።

እስኪ ከአጋሮችህ ጭብጨባ ፤ አጀብ ድንቅ የተሰኘ ሙገሳና ውደሳ ወዳስቸረህ ጉዳይ ልመለስ። የምናገረው እውነትና የሕዝብን ድምጽ ነው ብለሃል። እውነትን ቤተሰቦችህ በዚህ መልኩ ካስተማሩህ ምንም አልል ፤ ቤተሰቦቹን የሚያስድብ ልጅ አፍርታችሁአል ከማለት ውጪ። ይህ ጹሁፍ ኢ/ር ኃይሉን ወክሎ ለመናገር ከመፈለግ ሳይሆን እውነት ሲዛባ ዝምታን ካለመምረጥ መሆኑን በድጋሚ ላሳስበህ እወዳለሁ።

ይህ የተጋዳላይ ዳዊት 'ጹሁፍ' ከመነሻው ኢ/ር ኃይሉ ሻውል በአውራ ጎዳና መ/ቤት ሥራ አስኪያጅ ሳሉ ነው በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የጥፋት እጃቸውን ያነሱት ሲል የጻፈውን ሳነብ አላዋቂነት ደጉ አልኩ በልቤ። እንዳሻው የቅጥፈትን መአት ቢደረድሩ ታሪክ አዋቂም ቢሆኑ ማን ከልካይ አለና? እንደፊኛ እየተነፉ በሰማይ መንሳፈፍ እንጂ ። ስላቀረብከው አሉባልታ ቢያስፈልግ እንኩአ ራሳቸው መልስ ሊሰጡህ ይችላሉ ብዬ አገምታለሁ። እርግጥ ዳዊት ሰለአውራ ጎዳና መ/ ቤት ሲናገር ያለምክንያት አልዘገነነኝም። የርሳቸውን የስራ አፈጻጸም ሪፓርት ለመሙላት ሲደፋፈር ሳይ ጊዜ እንጂ። ሰው ሊያስብ የሚችለው የአቅሙን ታህል ብቻ ነውና ማንም አይፈርድበትም። ምናልባት ኢ/ር ኃይሉ አውራ ጎዳና መ/ ቤት በስራ ላይ ሳሉ የት እንደነበር አላውቅም። ግን በምርጫው ሰሞን የተፈጠረ ማስረጃ ልጥቀስልህ። ሰምኑን አብረሃቸው የሰነበትካቸው "መሪዎች" ካልደበቁህ ታውቀዋለህ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። በ 1997 ዓ.ም. ነው አውራጎዳና የምስረታ በዓሉን ሲያከብር በታሪኩ ውጤታማ ወይም መ/ቤቱን ስኬታማ ያደረጉ ኃላፊዎቹን ሲመርጥ ቁጥር አንድ ያደረገው አንተ የምትጠላቸው ኢ/ር ኃይሉ ሻውልን ነው።

እንግዲህ ይህን ተከትሎ በወቅቱ እርሳቸው ከሰራተኛው ለቀረበላቸው ጥሪ የሰጡት መልስ ለዚህ አስተያየት ፍጆታ ስለማያሻ አልፈዋለሁ። ማወቅ ከፈለክ ግን ብትጠይቅ ይነግሩሃል ወዳጆችህ በወቅቱ የሆነውን እንደሚያውቁ አውቃለሁና። ምናልባት ይህን መሰል ስሜት እንዲያድርብህ ያደረገህ የተሰለፍክበት ጎራ ግፊት ብቻ ሳይሆን የትምህርት ጉድለት ይኖርበታል እንደሚሉ አንዳንድ ሰዎች አላማህም። እንደምንም ብለህ ማትሪክ ብትወስድ ትጠቀማለህ እንጂ አትጎዳም የሚለውን ምክሬን ግን መለገስ እወዳለሁ።

በዚያ አዲስ የፈጠራ ባለቤትነት መብት ባስገኘልህ 'ጹሁፍህ' መርዝ እንደላሰች ውሻ ሁሉንም መልከፍ ለምን እንደመረጥክ አላውቅም። ይህ መሰሉ ችግር ብዙውን ጊዜ ሠው ሲጽፍ አይቶ መጻፍ አያቅተኝም ከሚል ስሜት የሚመጣ ይመስለኛል። በመጀመሪያ ለመጻፍ ስትወጥን የምትጽፈውን ማወቅ ደግ ነው። ከኢ/ር ኃይሉ ተነስተህ ለምን ዶ/ር ታዬን አይቼ ትላለህ ። የሌሎቹ የኪል ባልንጀሮችህ የዶ/ር ታዬን ወደ ትግሉ መግባት ለምን እንዳልወደዱ ይገባኛል።

ለነርሱ ቦታ አላጣም። አንተ ግን ዶ/ር ታዬ ማን እንደሆነ ታውቀዋለህ ያውቅሃል። ከበረታህ እንደምንም ብለህ ዶ/ር ታዬ ፊት ቀመህ ይህችን ተናገር ከማለት ውጪ ምንም አልልም።

ኢ/ር ኃይሉን አሳንሳለሁ ብለህ የውስጥህን ስሜትም አወጣህ ። "መለስ ዜናዊ እንኩአን ለፐ/ር ዓሥራት ወልደየስ ፈቃድ ሰጥቶ ውጪ እንዲታከሙ ሲፈቅድላቸው" አልክ። እውነት መለስ ዜናዊ ለፐ/ር ዓሥራት ህክምና እንዲያገኙ የፈቀደው እንደማይተርፉ አውቀ መሆኑ ጠፋህና ነው ይሄን የምትለው? በዚያን ወቀት በርግጥ አንተ በፀረ መዐሕድ ዘመቻ በርትተህ እየሰራህ ስለነበር ላይዋጥልህ ይችላል። በዚህ ጉዳይ ከአንተና ከመሰሎችህ ውጪ ማን ነው ሃሰት የሚል?

የሚገርመው አንተ በመዐሕድ መሪዎች ላይ ታደርግ የነበረው ያንን የመሰለ ስም ማጥፋትና የጥላቻ ቅስቀሳ መለስ ብዬ እያስታወስኩ አሁን ስለቅኛዝማች ነቅዓጥበብ በቀለ ፤ ስለ አቶ ዓሊ እንድሪስና አቶ ወንዳየሁ ካሳ ተቀርቁሪ መስለህ በመጻፍህ ሳይሆን ስላሰብከው እንኩአ ላንተ እኔ አፈርኩ። እባክህ እነዚህ ሠዎች አንተ በምትኖርበት አሜሪካ አሉና እስኪ አስታውሳቸው ። ትዝ ይልህ ከሆነ በፊያሜታ ጋዜጣህ ላይ ስትጽፍ የነበረውን አትዘንጋ ፤ አንተ ሁሉን ብትዘነጋው ቦታውን ባላስታውስም "ዘማዊትዋ ፊያሜታ " በሚል ርዕስ የተጻፈብህንና ዝም እንድትል ያደረገህን ጹሁፍ ጉዳይ እዚህ አንስቼ ስሜትህን ዳግም ልጎዳ አልፈልግምና አልፈዋለሁ።

ሌላም ብለሃል ኢ/ር ኃይሉ ኅብረቱን አፍርሰዋል ስትል ከልካይ ህሊና አላገኘህም። ለነገሩ የለም አልሳተፍም ብሎ መቅረት ነው ወይስ ያንተ ልደቱ እንዳደረገው ሰብሰባው ውስጥ ገብቶ በቴፐ ካልቀዳሁ ብሎ አምባጉዋሮ ማንሳት ነው አፍራሽነቱ? መልሱን ላንተ እተዋለሁ። መቼም ዛሬ ላይ ቀመን ትላንት የልደቱን ጥያቄ እንቀበልም ያሉት የፓለቲካ ሰዎች ትልቅ ናቸው እላለሁ። አይዞህ ተጋዳላይ ዳዊት ልደቱ ስብሰባ አዳራሽ ይዞት የገባው ያንተን መቅረጸ ድምጽ እንደሆነና በመጀመሪያ ካንተ ጋር መዶለቱን በወቀቱ ሚስጢር ብለህ ተናግረሃልና አላወጣብህም።

ታድለህ አንዱን ይዘህ ሌላውን ለመጣል ፈጥርሃልና ስለማታውቀው የቅንጅቱ የምርጫ ቅስቀሳም አዋቂ ነኝ ብለህም ጽፈሃል። እባክህን ከመጻፍህ በፊት አብረውህ ያሉትን ጠይቅ። መጠየቅ አንተ በምትኖርበት ሃገረ አሜሪካ ቀርቶ እኛ በምንኖርባት ኢትዮጵያም ነውር አይደለም። ብትጠይቅ አትሳሳትም ነበርና ነው። ቅንጅቱ የምርጫ ቅስቀሳውን ያካሂድ የነበረው በኮሚቴ ነው። ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለሊቀመንበሩ ነው። ጹሁፎች በኮሚቴ ተዘጋጅተው ነበር

የሚቀርቡት። አንተ እንደምትለው ወይም ቢጤዎችህ እንደምታስቡት ማን በማን ትከሻ ወጣ? አንድም መድረክ ላይ  አልቀረቡም የምትላቸው ኢ/ር ኃይሉ በኢኮኖሚ ጉዳይ በተደረገ ክርክር መቅረባቸውን አስታውሳለሁ፤ መልስ ከሆነልህ።

ኢ/ር ኃይሉ እኮ ለዓመታት በመስዋዕትነት የተገነባ ድርጅት ለዚያውም አንተና መሰሎችህ ጭምር ትላንት በአንድ የወያኔ ጎራ ፤ ዛሬ ወጥታችሁ በሌላ ስም በመንገዱ ቆማችሁበት እየታገለ ለዚህ የበቃ ድርጅት ይዘው የተሰለፉ ናቸው። እኮ እንዴት በሌላው ትከሻ ልትል ደፈርክ? እየህ የሰው ልክ የሚባል ነገር አለ። ልክን ማወቅ ። አንተም ራስህን ከፍ አደረክና ሹመት ሰጪና ነሽ ሆነህ “ሊቀመንበር ማድረጋችን ለካስ ስህተት ነበር” አልክ። ገባህ አሁን የሰው ልክ? ልኬትህን የማወቅ? እንዲህ ከመሰለ ስህተት ያድናል። ማንስ ነው በማን ትከሻ የተንጠለጠለው?  እስኪ ምን አለ ከመንገዱ ዞር ብትሉ? ይህን እዚህ ላይ ልተወው።

በዚህ ‘ጽሁፍህ’ አንድም ቦታ ራስህን ሳትሆን ከሰው ሰው ስትንጠለጠል ለምን መጉዝ አደመረጥክ አላውቅም። ቅንጅቱ አዲስ አበባን እንዳይዝ የፈለጉት ድ/ር ብርሃኑ ከንቲባ እንዳይሆን ፈልገው ነው ስትልም መክሰስ አማረህ ። በእውነት እልሃለሁ ዶ/ር ብርሃኑ የጻፍከውን ሲያነብ እንደሚስቅብህና እንደሚታዘበህ አውቃለሁ። እንደውም ያንተ ልደቱ አበርትቶ የአዲስ አበባን መቀመጫ ለመረከብ ሲገፋ ነበር ። ምናልባት አንተንና መሰሎችህን ከሁለላ ይዞ ማለቴ ነው ። ነገር ግን ቅንጅቱ የከተማውን ነዋሪ ካነጋገረ በሁአላ ነው ያንን የወሰነው። በዚህ ክስህ ሳታውቀው ዛሬ እሞትለታለሁ የምትለውን ቡድን መሪ ሃሳብ መቃረንህ አልገባህ ይሆናል ፤ ታድለህ ። እዚህ ላይ አንኳኳ ይሄን ያነሳሁት ሳታውቅ ቀርተህ ይሆናል ብዬ እንዳልሆነ ልብ በል። ምክንያቱም ይሁንኝ ብለህ ታሪክንና እውነትን በማዛባት ለርካሽ የቡድነኝነት ስሜት ለማዋልና የሰዎችን አመለካከት ለማዛባት ወጥነህ ስለተነሳህ ነው። ለነገሩ እኮ የዶ/ር ብርሃኑን ከንቲባነት ስለመቃወማቸው ማስረጃ አቅርብ ብትባል ምን እንደምትል አንተን አይደለሁምና አላውቅም። ዳሩ አንተም አልተናገርክም ፤ እውነቱን ታውቃለህና።

ያንተ የቅርብ አለቃ የነበረው ልደቱ አያሌው የቅንጅት ሊቀመንበርነትን ቦታ ካጣን የአዲስ አበባ ከንቲባነት ለኔ ፓርቲ ይገባል ፤ ሊቀመንበራችን ዶ/ር አድማሱ ገበየሁ መሆን አለባቸው በማለት ያነሳውን ጠብ አላስታውስም ካልክ አልፈርድብህም። ያን ጊዜም እንዲሁ በልደቱ ፊና ጥግ ይዘህ ከነዶ/ር ብርሃኑ ጋር ትማዘዝ የነበረውን ጦር ሁሉም ያውቃልና እንለፈው ። ዛሬ ደግሞ ሌላ። በወቅቱም ኢ/ር ኃይሉም ይሁኑ ፕ/ር መስፍን የነበረውን ውዝግብ ለማርገብና ለመለወጥ ያደረጉትን ጥረት አንተ ብትክድ ማንም ያውቀዋል።እየህ የማያውቁትን ነገር የመጻፍ ትልቅ ጉዳት?

ፓርላማ አለመግባትንም ቢሆን እኮ እኒህ ስማቸውን የምታነሳቸው አንድ ግለሰብ ብቻቸውን አልወሰኑም ። ያንተዎቹ ባይብስ? ጥላቻ ጥሩ አይደለም ። ለዚያውም በዚህ ዕድሜህ። ፓርላማ እንዳይገባ በማድረግ “ለገባንበት አረንቋአ” ስትል ከሰስካቸው ። ትንሽ ዝቅ ብለህ “ለደረሰው ጉዳት ኃይሉ ሻውልና መለስ ዜናዊ በእኩል ደረጃ ተጠያቂ መሆናቸው የማይቀር ነው ” አልክ። የአራዳ ፓለቲከኛ አይደለህ እንዳትፎገርና የወያኔ ተቃዋሚ ለመባል የመለስን ስም አስገባህ ። “ምን ካሉ አይቀር …” እንደኛህን አውጀህ አትገባም እንዴ ? አይዞህ አኛ እያወቅን እንዳላወቅን እናልፋልሃለንና ሌላም ክስ ካለህ ጨምርበት።

ተጋዳላይ ዳዊት ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ ካልሆነብህ በቀር ከንግዲህ ብስል ከቀሊል ተለይቱአል። በትግሉ የጸና ይቀጥላል። አንተ ብዙ አልከ እንጂ ከቶ አንተንም የሚሸከም ጫንቃ ይኖራል ብለህ ለመጠበቅህ አዘንኩልህ – አፈርኩምም ። ከእንግዲህም አውሮፓና አሜሪካ ተቀምጦ በቀላጤ የስራ ማቆም አድማ በመጥራት ፤ በኢንተርኔት ካላንደር አሳትሙ እያሉ ሰው ማሳሰር የለም። ለጥናት ለምርምር እያሉም ከሃገር ሃገር እየዞሩ የመዋጮ ገንዘብ መብላት ፤ ሃገር ውስጥ ስራ እናሰራለን እያሉ ገንዘብ አስልኮ የተላከላቸው ይዘው ጠፉ ማለት ማከተሙ ጎራችሁን ቢያንጫጫ ማንም አይፈርድም።” ሌባ ሲሰርቅ ሳይሆን ሲካፈል ነው የሚጣላው “የሚባለው ብሂል ገቢር እንዳይሆንባችሁ በእጃችሁ የገባውን አደራ ስትካፈሉ እንዳትጣሉ ብዬ የወንድምነቴን ባልመከርህ አልፎ እንዳትወቅሰኝ ህሊናዬ ፈራ።

ከእንግዲህ ለነጻነት ትግሉ የፀኑ የአንድነት ኃይሎች የሚያሰጋቸው ላይኖር ይችላል ። የጠላት ኃይሉ ወደ አንድ ኮሮጆ ተጠቃሎ ገብቶአልና ኃይልና አንድነታቸውን በአንድ አድርገው ከመታገል ውጪ ወደሁላ መሂድ የለም።ወንፊቱ እያንገዋለለ ከሚተፋው በቀር ባቡሩ ግስጋሴውን ይቀጥላል በሚል ተስፋዬ ሙሉዕ ነው ።”እንቶኔ ለእንቶኔ አብረህ አዝግም” ልል አሰብኩና ለምን እንደሆነ አላውቅም አንተን መሆን እንዳይሆን ብዬ ተውኩት።

በዚህ ልሰናበትህ መሆኑ ነው። ታዲያ አንድ ነጥብ ላክል ፈለኩኝ። “አንድ ዐይና በአፈር አይጫወትም ” የሚለውን ርዕስ ለምን እንደመረጥኩ ። አደራ በሌላ እንዳትወስድብኝ። በአምላክ ስራ ለመግባትም አይደለም። ነገር ግን የርዕሴ መነሻም ይሁን መድረሻ ሰበብ አንድ ብቻ ነው። ይሂውም አንተ ይሄን ደፍረህ በአደባባይ ስትጽፍ የቀምከበትን ባላ የዘነጋህው መስሎኝ እንጂ። የትላንቱ የወያኔ ጠበልህ ሳይለቅህ ቢያድልህ የነጻነቱን ቀንዲልና የአንድነቱን ኃይል ልትረዳ ሲገባህ ካልሆነልህ አፍህንና እግርህን ሰብስበህ መቀመጥ ሲኖርብህ ወደዚህ ተግባር በመሰማራትህ ነው ይህን የቀየ ቁምነገር አዘል አባባል ያስታውሰኝ። መንፈስህን አረጋጋና ደግመህ አንብበው። አስታወስከኝ?

ታሪኩ – ከደሮ ማነቂያ